<u>አንድ ሰው ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ይዞ መግባት የሚችላቸው ዕቃዎች ዝርዝር</u>

1. ወደ አገር ማስገባት የሚችሉት የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ከየአይነቱ አንድ(1 Pecise) ወይም እንደ ዕቃው ባህሪ በሴት አንድ (One Set) ብቻ መሆኑ፣
2. ለአንድ አይነት ዕቃ ከአንድ Piece 1 Set) በላይ ከሆነ በፍተሻ ተረጋግጦ የዕቃው ቀረጥና ታክስ መክፈው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ ቅጣት ከፍሎ እንደሚስተናገዱ ከባለሥልጣን መ/ቤታችን በወጣው የመመሪያ ቁጥር 46/ የሚስተናገዱ መሆኑ፣
3. ተሽከርካሪን አስመልከቶ ወደ አገር ማስገባት የሚችሉት ተመላሽ ኢትዮጵያን እና ትውልደ ኢትዮጵያን አምስት አመትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በውጭ አገር ቆይተው ጠቅለው ለሚመለሱት አንድ የቤት አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ ከፍለው የሚስተናገዱ ሲሆን፣
4. በኢንቨስትመንት መስክ የተሰማሩ ባለሀብቶች እስከ ብር 5,000,000.00 /አምስት ሚሊዮን ብር/ በአገር ውስጥ ኢንቨስት ሲያደርጉ እስከ 10,000.00 USD/አስር ሺ ዶላር/ የሚያወጣ የግል መገልገያ ተሽከርካሪን ሳይጨምር ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንደሚችሉ ተቀምጧል፡፡

ሆኖም በቅ/ጽ/ቤታችን መስተንግዶ ለማግኘት የሚቀርቡ ተመላሾችም ሆኑ ኢንቨስተሮች በውጭ አገር ከሚኖሩበት ኤምባሲ የግል መገልገያና ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት እንደሚችሉ በተገለፀላቸው መሠረት የመጡ መሆኑን በመግለፅ መስተንግዶ የሚጠይቁ ሲሆን መመሪያው የተቀየረ ለመሆኑ ማብራሪያ ሲሰጣቸው ከሚኖሩበት አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ /ቆንሱላ ጽ/ቤት/ ለግልና ለቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ሙሉ ቀረጥና ታክስ ስለመከፈሉ መሆኑን በመግለፅ ከፍተኛ ቅሬታ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ የተሟላ መረጃ ባለማግኘት በሚፈጠረው የአገልግሎት መዘግየት የደንበኞች ውጣ ውረድ በስራችን ላይ ከሚፈጥረው ችግር ባሻገር በተቋሙ እና በአገራዊ ገፅታ ግንባታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ በመሆኑ ዳይሬክቶሬቱ ለሚመለከታቸው ሚ/ር መ/ቤቶች ይህንኑ እንዲያሳውቅ ቢደረግ፣ በተጨማሪም በገቢ ለልማት ፕሮግራም፣ ባለሥልጣኑ በሚያሳትማቸው ህትመቶች እና በድህረ ገፅ ወቅታዊ መረጃ ቢተላለፍ እና ማንኛውም ተጠቃሚ ማግኘት እንደሚችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሰሩ እንጠይቃለን፡፡

ሆኖም በቅ/ጽ/ቤታችን መስተንግዶ ለማግኘት የሚቀርቡ ተመላሾችም ሆኑ ኢንቨስተሮች በውጭ አገር ከሚኖሩበት ኤምባሴ የግል መገልገያና ተሽከርካሪ ቀረጠና ታክስ ነፃ ማስገባት እንደሚተሉ በተገለፀላቸው መሠረት የመጡ መሆኑን በመግለጎ መስተንግዶ የማጠይቁ ሲሆን ኤምባሲ/ቆንሱላ ጽ/ቤት /ለግልና ለቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች ሙሉ ቀረጥና ታክስ ስለመከፈሉ መሆኑን በመግለፅ